# ደንብ ቁጥር 184/2017

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድን ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ መምጣቱ በመደበኛው የንግድ ሥርዓት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑን በመገንዘብ ይህንን ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ በሥርዓት ካልተመራ በከተማ ውበትና ገጽታ፤ በከተማ ጽዳት፤ በትራፊክ ፍሰትና እንቅስቃሴ፤ በኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት እና በከተማዋ ሰላምና ፀጥታ አጠባበቅ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል በመሆኑ፤

መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማግኘትና የሚያስከትላቸውን ችግሮች መቅረፍ የሚቻለው ዘርፉ ህጋዊ ሆኖ በሥርዓት ሲመራ በመሆኑና ዘርፉን ሥርዓት በማስያዝ በዘርፉ የተሰማሩ ሰዎች ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበረው መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣው ደንብ ቁጥር 88/2009 አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም በማድረግ መተካት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀፅ 94 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድን ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ ቁጥር 184/2017 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

   የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. "ከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
   2. "የንግድ ሕግ" ማለት የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ነው፤
   3. "አዋጅ" ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ነው፤
   4. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድ ቢሮ ነው፤
   5. "ጽሕፈት ቤት" ማለት እንደአግባቡ የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደር የንግድ ጽህፈት ቤት ነው፤
   6. "ጎዳና" ማለት ዋና መንገድ፤ መጋቢ መንገድ፣ ቀለበት መንገድ፣ አደባባይ፤ የእግረኛ መንገድ፤ የመንገድ አካፋይ፣ የመንገድ ዳርቻ ሲሆን ክፍት ቦታዎችን ይጨምራል፤
   7. "መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ" ማለት በንግድ መዝገብ ሳይመዘገብና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያወጣ ወይም ቋሚ የንግድ ቤት ወይም ቦታ ሳይኖረው በዚህ ደንብ መሠረት በተፈቀደ ቦታ እና ቀናት በጎዳና ላይ እስከ ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ በሚገመት በአነስተኛ ካፒታል ሸቀጦች እና አገልግሎቶችን ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለሽያጭ በማቅረብ የሚሠራ የንግድ ሥራ ዓይነት ነው፤
   8. "መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ነጋዴ" ማለት በዚህ ደንብ መሰረት በተፈቀደ ቦታ፤ ቀን እና ሰዓት የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚያካሂድ ሰው ነው፤
   9. "እሁድ ገበያ" ማለት በተመረጡ ጎዳናዎች ወይም ክፍት ቦታዎች አምራቾች፣ አርሶ አደሮች፣ ጅምላ ነጋዴዎች እና በኢንተርፕራይዝ የተደራጁ ማህበራት ቅዳሜና እሁድ ምርት፣ ሸቀጣ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት ግብይት የሚያካዱበት ቦታ ነው፤



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

10."መዝገብ" ማለት በመደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚመዘገቡበት በቢሮው የሚዘጋጅ ባህረ መዝገብ ነው፤

11."ቋሚ የመነገጃ ቦታ" ማለት ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሲባል ተለይቶ ለንግድ የተመደበ ወይም የተዘጋጀ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ቀን፣ ሰዓት እና የሥራ ዘርፍ ወይም መስክ ፕሮግራም የወጣለትና በዚሁ መሠረት ሳይቋረጥ ቦታው ለልማት ወይም ለሌላ አገልግሎት እስኪፈለግ ድረስ በጊዜያዊነት መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚከሄድበት ቦታ ነው፤

12."ጊዜያዊ የመነገጃ ቦታ" ማለት ለንግድ ሥራ ቀንና ሰዓት ፕሮግራም ያልተያዘለት የንግድ ዘርፍ ወጥቶለት ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጁ ጎዳናዎች በጊዜያዊነት መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚከሄድበት ቦታ ነው፤

13."መደበኛ ያልሆነ ጽዳት" ማለት የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በመደበኛነት በዕቅድ ከሚያፀዳቸው የተለያዩ ቦታዎችና ጎዳናዎች በተለየ ሁኔታ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ የሚከሄድባቸውን ሥፍራዎች በሙሉ ሥራውን ተከትሎ ግብይቱ በተወሰነለት ዕለትና ሠዓት ከተከናወነ በኋላ በልዩ ሁኔታ የሚከሄድ የጽዳት ሥራ ነው፤

14."ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ" ማለት በደረት ላይ የሚንጠለጠል ሆኖ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ለሚሠራ ነጋዴ በበጀት ዓመቱ የተሰጠ ወይም የታደሰ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የሚታደስበት ጊዜ ያላለፈበት ፈቃድ ወይም መታወቂያ ወይም መለያ ነው፤

15."አስተዳደራዊ እርምጃ" ማለት ይህን ደንብና ደንቡን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ በሚገኝ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ነጋዴ ላይ እንደ አስፈላጊነቱ በቢሮው ወይም በክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ወይም በወረዳው ጽሕፈት ቤት አማካይነት ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ፈቃድ እስከ መሠረዝ የሚወሰድ እርምጃ ነው፤

16."ግብረ ኃይል" ማለት መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥርዓት ባለው መልኩ እንዲካሄድ በበላይነት የሚመራ፣ እና ክትትል ድጋፍ የሚያደርግ አካል ነው፤

17."ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፤

18. በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡



Addis Ababa City Administration Justice Bureau

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ንግድ ሥራ ላይ በተሠማራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>ዓላማ</u>

የዚህ ደንብ ዓላማ፡-

1. መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚመራበትን ሥርዓት በመዘርጋት ለኢኮኖሚውና ለማኅበራዊ እንቅስቃሴ አጋዥ እንዲሆን ማስቻል፣
2. በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች በመፍታትና በቂ ድጋፍ በማድረግ በቀጣይ ወደ መደበኛ ንግድ ሥርዓት እንዲገቡ ማስቻል ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ምዝገባ እና ፈቃድ አሰጣጥ</u>

5. <u>መዝገብ ስለማደራጀት</u>

1. መደበኛ ባልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የሚመዘገብበት መዝገብ በዚህ ደንብ ይደራጃል፣
2. ቢሮው በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ባልሆነ የጎዳና ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማናቸውንም ሰው ይመዘግባል፡፡

6. <u>ስለመመዝገብ</u>

1. ማንኛውም ሰው በመዝገብ ሳይመዘገብ በየትኛውም ቦታ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፤
2. የእሁድ ገበያ በመባል የሚታወቁት እና የትራፊክ ፍሰት የማይበዛባቸውን ቦታዎች ለጊዜው በመዝጋት በሳምንት ቅዳሜና እሁድ መደበኛ ባልሆነ ጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚሰማራ ሰው በዚህ ደንብ መሰረት መመዝገብ አለበት፤
3. የኑሮ ውድነትን ለመቅረፍና የገበያውን ዋጋ ለማረጋጋት በእሁድ ገበያ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ለተጠቃሚው በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ከቢሮው ወይም ከጽህፈት ቤቶች ጋር በትስስር የንግድ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች በዚህ ደንብ መሰረት መመዝገብ አለባቸው፤
4. ማንኛውም ሰው በመዝገብ የሚመዘገበው በሚሠራበት አካባቢ በሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ነው፤



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

5. ማንኛውም ሰው በመዝገብ የሚመዘገበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

7. <u>በመዝገብ ስለሚገቡ ጉዳዮች</u>

መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ መዝገብ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

1. የነጋዴው ስም ከነአያት፤
2. ዜግነት፤
3. የመኖሪያ አድራሻ፤
4. የጎዳና ላይ ንግዱ የሚካሄድበትን አድራሻ፤
5. የንግዱ የሥራ ዓይነት ወይም መስክ፡፡

8. <u>የምዝገባ መስፈርት</u>

በመደበኛ ባልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ አመልካች የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡-

1. በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተነሳው 2 (ሁለት) ጉርድ ፎቶ ግራፍ፤
2. በከተማ አስተዳደሩ ነዋሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ ዲጂታል መታወቂያ፤
3. ከግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የተሰጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
4. ዕድሜው 18 ዓመት የሞላው መሆን ማረጋገጫ ፤
5. በመደበኛ ንግድ ሥራ ላይ ወይም ሌላ ማንኛውም ሥራ ላይ ያልተሠማራ እና ሥራ አጥ መሆኑን በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ከሚኖርበት ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የጽሁፍ ማስረጃ፤
6. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) ድንጋጌዎች ቢኖሩም በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በእሁድ ገበያ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማቅረብ ከቢሮው ወይም ከጽህፈት ቤት ጋር ትስስር የፈጸመ ከሆነ የትስስር ሰነዱን በማቅረብ ብቻ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

9. <u>ስለፈቃድ አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም መደበኛ ባልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት ቢሮው ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በማያያዝ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት ማቅረብ አለበት፤



Addis Ababa City Administration Justice Bureau

2. ማንኛውም ለምዝገባ የቀረበ ማመልከቻ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ከተገኘ የወረዳው ጽሕፈት ቤት አግባብ ባለው ደንብ መሠረት የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል መዝግቦ መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ነጋዴ ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ይሰጠዋል፤
3. ቢሮው ለምዝገባ አገልግሎት የሚውሉ ወጥ ቅፆችን ያዘጋጃል፤ ለወረዳ ጽሕፈት ቤት ይልካል፤
4. ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ደረጃውን የጠበቀ እና በቀላሉ ሊዘጋጅ የማይችል መሆን ይኖርበታል፡፡

10.<u>የምዝገባ መረጃዎችን ስለማስተላለፍ</u>

1. በዚህ ደንብ መሠረት ምዝገባ ያደረገ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ለዚህ ጉዳይ በሚዘጋጅ ቅጽ አማካይነት የምዝገባ መረጃዎችን በየዕለቱ ለክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ያስተላልፋል፤ የክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት በሚቀጥለው ቀን ለቢሮው ያስተላልፋል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምዝገባ ያደረገ የወረዳ ጽህፈት ቤት የምዝገባ መረጃዎችን ለክትትል እንዲያመች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤
3. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተላለፉለትን የምዝገባ መረጃዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መዝግቦ ይይዛል፤ እንደአስፈላጊነቱ በሚዘጋጅ ሶፍትዌር ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ላይ ይመዘግባል፡፡

11.<u>እውቅና ስለመስጠት</u>

በዚህ ደንብ መሠረት ተመዝግቦ ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ወይም ገበያ ለማረጋጋት በእሁድ ገበያ ላይ ትስስር የተፈጠረለት እና በተፈቀደ ቦታ ላይ የሚሠራ ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቶታል፡፡

12.<u>ስለምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ</u>

1. ማንኛውም ሰው መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራውን ለማካሄድ ከተመዘገበበት እና ከተመደበበት የሥራ ቦታ አካባቢ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ አካባቢ ለመለወጥ ከፈለገ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ (3) እና አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት በቅድሚያ ያደረገውን ምዝገባ ማሰረዝና ከወረዳው ጽሕፈት

ቤት የተሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት መመለስ አለበት፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ምዝገባው የተሰረዘና ፈቃዱን የመለሰ የጎዳና ላይ ነጋዴ መሸኛ ወረቀት በመውሰድ ወደ መረጠው አካባቢ የሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት በመሄድ መሸኛውን አቅርቦ መመዝገብ ይችላል፤
3. ማንኛውም ሰው ተመዝግቦ የሚሰራውን የንግድ መስክ ዓይነት መለወጥ ወይም ማሻሻል ከፈለገ የተመዘገበበት ወረዳ ጽሕፈት ቤት በመቅረብ በቢሮው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የሚሠራውን የንግድ መስክ ዓይነት መለወጥ ወይም ማሻሻል ይችላል፤
4. የምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ስለመቅረቡ እና ተቀባይነት ስለማግኘቱ የወረዳው ጽሕፈት ቤት ማረጋገጫ መስጠት እና ተቀባይነት ያገኘበትን ቀን፣ ስለምዝገባው ለውጥ ወይም ማሻሻያ በዝርዝር በመግለጽ ለአመልካቹ እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 13. ደረት ላይ ስለሚንጠለጠል ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት የተሰጠ ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ በዚህ ደንብ መሰረት ካልተሠረዘ እና በየዓመቱ የታደሰ ከሆነ የጸና ይሆናል፤

2. በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የበጀት ዓመቱ ካበቃ በኋላ ባሉት 2 ወራት ጊዜ ውስጥ ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ እስከ ነሀሴ 30 ቀን ድረስ ግብር አስከፋይ መስሪያ ቤት ግብራቸውን ወስኖ እንዲከፍሉ ያደርጋል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የፈቃድ እድሳት በበጀት አመቱ ከሀምሌ 1 ጀምሮ እስከ ታህሳስ 30 ድረስ ከግብር አስከፋይ መስሪያ ቤት ክሊራንስ በማቅረብ ተገቢውን ክፍያ ከፍሎ በየአመቱ ፈቃዱን ለሰጠው ወረዳ ጽህፈት ቤት ቀርቦ መታደስ አለበት፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በበጀት አመቱ ፈቃዱን ወይም መታወቂያውን ያላሳደሰ መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ ክፍያ እጥፍ በመክፈል ፈቃዱን ማሳደስ ይችላል፤



Addis Ababa City Administration Justice Bureau

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ፈቃዱን ወይም መታወቂያውን ያላሳደሰ ሰው ከመዝገብ ይሰረዛል፤ ተመዝጋቢው የተሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ መመለስ አለበት፤ ሳይመልስ ቢቀር በእጁ እንዳለ እንደተሠረዘ ይቆጠራል፡፡

14.ምትክ ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ስለመስጠት

1. የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ምዝገባ ያደረገ ማንኛውም ሰው የተሰጠው ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት እንደሆነ ቀደም ሲል ለሰጠው የወረዳ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ በማመልከት ምትክ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፤
2. ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃዱ የተበላሸበት ማንኛውም ሰው ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የተበላሸውን ይመልሳል፤
3. የወረዳው ጽህፈት ቤት ማመልከቻ ሲቀርብለት ለጠፋው ወይም ለተበላሸው ፈቃድ ወይም መታወቂያ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ምትክ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ይሰጣል፡፡

15.የተመዘገበና ተንጠልጣይ ፈቃድ የተሰጠው ሰው መብትና ግዴታ

ማንኛውም በዚህ ደንብ መሰረት የተመዘገበና ደረት ላይ ተንጠልጣይ ፈቃድ የተሰጠው ሰው፡-

1. መብቶች
   ሀ) በመዝገብ ያስመዘገበውን እና የተፈቀደለትን የጎዳና ላይ የንግድ ሥራ ማካሄድ፤ ፈቃድ መውሰድ፣
   ለ) የተሰጠው ፈቃድ ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ምትክ መውሰድ፣
   ሐ) የሚነግደውን የጎዳና ላይ የንግድ ሥራ ዘርፍ እና የሚነግድበት ቦታ ወይም አካባቢ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት አሳውቆ የመለወጥ፣ የማሻሻል፣
   መ) የመነገጃ አካባቢውን ወይም የሚነግድበትን የሥራ መስክ መሰረት በማድረግ አግባብ ባለው ህግ መሰረት በማኅበር የመደራጀት፤
2. ግዴታዎች እና ክልከላዎች
   ሀ) የወረዳው ጽህፈት ቤት በፈቀደለትና በመደበው ቦታ፣ ዕለት፣ ሰዓት፣ እና የሥራ ዘርፍ ላይ ብቻ መሥራት አለበት፤
   ለ) መደበኛ ላልሆነ ንግድ ሥራ የሚይዛቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች፣ የገዛበትን ህጋዊ ደረሠኝ ማቅረብ አለበት፣



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ Addis Ababa City Administration Justice Bureau

ሐ) ለሸማቹና ለተጠቃሚው ተገቢውን ክብር መስጠት አለበት፣

መ) ከመዝጋቢው አካል የተሰጠውን ደረት ላይ ተንጠልጣይ ፈቃድ በሥራ ላይ በሚሆንበት ጊዜ አንገቱ ላይ በማጥለቅ በግልጽ እንዲታይ ማድረግ፣

ሠ) በመዝጋቢው አካል መረጃ ሲጠየቅ መረጃውን ወዲያው መስጠት አለበት፣

ረ) የጎዳና ላይ ንግድ ሥራውን ሲጨርስ አካባቢውን በአግባቡ ማጽዳት አለበት፣

ሰ) የአካባቢውን ንጽህና፣ ፀጥታና ደህንነት መጠበቅ አለበት፣

ሸ) ባልተፈቀደ ቦታ መነገድና የትራፊክ እንቅስቃሴ ማወክ የለበትም፡፡

ቀ) በውክልና መመዝገብ የተከለከለ ነው፣

በ) ለጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚይዛቸው ዕቃዎችን ጥራት፣ መጠን፣ ይዘት መለወጥ ወይም ማጓደል፣ ሸማቹን እና ተጠቃሚውን ማታለል የለበትም፣

ተ) የተሳሳቱ ወይም ተመሳስለው የተሰሩ ምርቶችን መሸጥ የለበትም፣

ቸ) የብቃት ማረጋገጫ ወይም መስፈርት የሚያስፈልጋቸውን ምርቶች መያዝ የለበትም፣

ኀ) የተሰጠውን ደረት ላይ ተንጠልጣይ ፈቃድ እንዳይበላሽ በጥንቃቄ መያዝ፤ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት የለበትም፡፡

16. ስለ አገልግሎት ክፍያ

ቢሮው መደበኛ ያልሆነ ለጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ምዝገባ እና ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ወይም መታወቂያ ለመስጠት ወይም ለማደስ እና ለተያያዥ አገልግሎቶች የሚጠየቁ የአገልግሎት ክፍያዎችን እያጠና ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

17. ከመዝገብ ስለመሰረዝ እና አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

1. በመደበኛ ያልሆነ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ከመዝገብ ይሰረዛል፡-

ሀ) የንግድ ሥራውን ከተወ፣

ለ) ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ፣

ሐ) ሐሰተኛ መረጃ ወይም ሰነድ አቅርቦ መመዝገቡ ከተረጋገጠ፣

መ) ከተፈቀደለትና በመታወቂያው ላይ ከተገለጸው ቦታ ወይም ቀን ወይም ሰዓት ወይም የጎዳና ላይ ንግድ የሥራ ዘርፍ ውጪ ወይም ባልተፈቀደ ሥራ ላይ ተሠማርቶ ከተገኘ፣



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ Addis Ababa City Administration ... Bureau

ሠ) ቢሮው ወይም የወረዳ ጽሕፈት ቤቱ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች በትክክል እና በወቅቱ ያላቀረበ እንደሆነ፣

ረ) የሸማቹን የጤናና የጽዳት አጠባበቅ፣ የአካባቢ እንክብካቤ፣ የንግድ ዕቃውን ጥራት ወይም አይነት ደረጃ ካጓደለ ወይም ሌላ ሕገ ወጥ ተግባር ከፈጸመ ወይም በኮንትሮባንድ የገቡ ዕቃዎች ወይም የራሱ ያልሆነውን በአዋጁ መሠረት በመደበኛ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ነጋዴ ዕቃ ይዞ ከተገኘ፣

ሰ) ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ካልታደሰ፣

ሸ) ሸማቹን በማታለል ወይም በማሳሳት ተግባር ላይ ከተገኘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ ይህን ደንብ የጣሰ እንደሆነ፤

2. ቢሮው መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድን ሥርዓት ለማስያዝ በሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር ይህንን ደንብ ተቃራኒ በሆነ መንገድ የጎዳና ላይ ንግድ የሚያከናውን ማንኛውም የተመዘገበና ፈቃድ ያለው ሰው ሲያገኝ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

3. ማንኛውም የጎዳና ላይ ነጋዴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከቱ ጥፋቶችን መፈጸሙ ሲረጋገጥ፡-

ሀ) ቢሮው ወይም የወረዳ ጽህፈት ቤት አጥፊውን መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ነጋዴ ከመዝገብ በመሰረዝ ስለመሰረዙ በጽሁፍ ያስታውቀዋል፣

ለ) ፈቃዱ የተሰረዘበት የጎዳና ላይ ነጋዴ ቢሮው ወይም የወረዳው ጽህፈት ቤት የሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ተመላሽ ማድረግ አለበት፣

ሐ) የንግድ ዕቃዎቹንና የመገልገያ ዕቃዎቹን በማንሳት የጎዳና ላይ ንግድ ሲሰራበት የነበረውን የመነገጃ ቦታ ይለቃል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

## ክፍል ሦስት

## ለጎዳና ላይ ንግድ የሚፈቀዱ የሥራ መስኮች፣ የመነገጃ ቦታዎች እና ወደ መደበኛ ንግድ ሥራ ስለማሸጋገር

18.ለጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ስለሚፈቀዱ የሥራ መስኮች

1. መደበኛ ያልሆነ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የተሰማራ ሰው የሚሰራው የንግድ ሥራ ዓይነት፣ የሥራ መስክ ወይም የሥራ ዘርፍ ዝርዝር በህግ የተፈቀደ መሆን ይገባዋል፤
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መደበኛ ያልሆነ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራ ሰዉ ለመሥራት የሚፈቀዱ የንግድ ሥራ ዓይነቶች ወይም መስኮች ቢሮው በየጊዜው እያጠና በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤
3. ቢሮው በዚህ አንቀጽ 6 እና 13 መሰረት መመዝገብና ፈቃድ ማውጣት የማያስፈልጋቸውን ጥቃቅን መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ አይነቶች በመመሪያ ሊወስን ይችላል፤
4. በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የተሰማራ ሰዉ የሚሰራዉ የንግድ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እና መስፈርት የማያስፈልገዉ የንግድ ሥራ ዓይነት መሆን አለበት፡፡

19.የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ለማካሄድ ስለሚፈቀድባቸው ቦታዎችና የማከናወኛ መገልገያዎችን ስለመወሰን

1. የጎዳና ላይ ንግድ ለመሥራት የመነገጃ ቦታ ሊሰጥ የሚቻለው ከሚከተሉት ምድቦች በአንዱ ይሆናል፡-
   ሀ) በቋሚ የመነገጃ ቦታ፣
   ለ) በጊዜያዊ የመነገጃ ቦታ፣
   ሐ) የቅዳሜና የእሁድ ገበያ፤
2. የጎዳና ላይ የንግድ ሥራ መሥራት የሚቻለው የከተማውን ዋና ዋና መንገዶች፣ የከተማውን ውበት በማይነካ ብሎም ደህንነት በጠበቀ መልኩ በሚመለከታቸዉ አካላት በጥንቃቄ ተለይተው በሚፈቀዱ ጎዳናዎች ላይ በግብረ-ኃይሉ ይሁንታ ሲያገኝ ብቻ ይሆናል፤
3. መደበኛ ያልሆነ ለጎዳና ላይ ንግድ የተፈቀዱ ጎዳናዎችን በሚመለከት ቢሮው የመለያ ምልክቶችን ያስቀምጣል ወይም ይተክላል ወይም እንዲከለሉ ያደርጋል፤



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ
Addis Ababa City ... Bureau

4. መደበኛ ያልሆነ ለጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚፈቀዱ ቦታዎች ከትራፊክ እንቅስቃሴ እና ፍሰት ማሳለጥ አንፃር፤ ከመንገድ ሊኖራቸው የሚገባውን ርቀት ፤ ለሸማቾች የሚኖራቸውን አመችነት እና ቅርበት፤ የመደበኛ ነጋዴዎችን ገበያ አለአግባብ እንዳይሻማ ከመከላከል አንፃር እና የመሳሰሉትን መስፈርቶች ወይም ስታንዳርድ ይሆናል፤

5. ቢሮው የንግድ ሥራውን ዓይነትና ባህሪይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለጎዳና ላይ የንግድ ሥራ ማከናወኛ የሚውሉ ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ ተገጣጣሚ የከተማውን ውበት ማስጠበቅ የሚችሉ እና አትምን ያገናዘቡ መገልገያዎች ዓይነትና ዲዛይናቸውን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

20.ወደ መደበኛ የንግድ ሥራ ሽግግር ስለ ማድረግ

1. በዚህ ደንብ መሰረት መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በሥራ ላይ ከተሰማራበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2 (ሁለት) ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ የሀብት መጠን ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የደረሰ ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት መዘዋወር አለበት፤

2. ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት ስለሚዘዋወርበት ሁኔታ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

21.ድጋፍና ቁጥጥር ስለማድረግ

1. የወረዳው ጽህፈት ቤት የቁጥጥር ባለሙያ የተመዘገበና ደረት ላይ የሚንጠለጠል ፈቃድ ወይም መታወቂያ የተሰጠው ሰው ግዴታዎችን በትክክል መወጣቱንና በዚህ ደንብ መሠረት ሥራው መካሄዱን ለማረጋገጥ ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋል፤

2. በቢሮው ወይም በጽሕፈት ቤቱ ለቁጥጥር ሥራ የሚሰማራ የቁጥጥር ሠራተኛ የተሰጠውን የመስሪያ ቤት መታወቂያ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራው ሰው በቅድሚያ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ግብረ ኃይል መቋቋም፣ ድጋፍ፤ ክትትል እና የባለድርሻ አካላት ሚና

22.ግብረ ኃይል ስለማቋቋም

1. መደበኛ ያልሆኑ የጎዳና ላይ ንግድን ሥርዓት ለማስያዝ የሚደረገውን ተግባር ከግብ ለማድረስ የሚሰሩ አስተግባሪ አካላትን በበላይነት አቀናጅቶ የሚመራ ግብረ ኃይል በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Justice Bureau

2. የግብረ ኃይሉ ተጠሪነት ለከተማው ከንቲባ ይሆናል፡፡

23.<u>የግብረ ኃይሉ አባላት አሰያየም</u>

1. የግብረ ኃይል አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) የከተማው ምክትል ከንቲባ ........................................ ሰብሳቢ፣

ለ) የንግድ ቢሮ ኃላፊ ........................................ አባልና ፀሐፊ፣

ሐ) የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ........................................ አባል፣

መ) የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ........................................ አባል፣

ሠ) የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ........................................ አባል፣

ረ) የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ........................................ አባል፣

ሰ) የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ........................................ አባል፣

ሸ) የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ........................................ አባል፣

ቀ) የምግብና መድሃኒት ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ........................................ አባል፣

2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአባላቱ ቁጥር በከንቲባ ሊጨምር ይችላል፡፡

24.<u>የግብረ ኃይሉ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ግብረ ኃይሉ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የዚህን ደንብ አፈጻጸምና አተገባበር በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
2. የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ የፖሊሲ ምክረ ሀሳቦችን ያቀርባል፣
3. በባለድርሻ አካላት መካከል ውጤታማ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
4. የጎዳና ላይ ንግድ የሚፈቀዱ ቦታዎችን አስመልክቶ በቢሮው ወይም በሚመለከታቸው አካላት ተዘጋጅተው የሚቀርቡ መስፈርቶች እና ስታንዳርዶች ላይ ተወያይቶ ያጸድቃል፣
5. የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ እንዲውሉ በሚመለከታችው አካላት ተለይተውና ተዘጋጅተው በሚቀርቡ የመነገጃ ቦታዎች ላይ ተወያይቶ ይወስናል፣
6. የደንቡ አስፈጻሚ አካላት በዚህ ደንብ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት አፈጻጸም አስመልክቶ ወቅታዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

ይገመግማል፣ የአፈጻጸም ድክመት ባሳዩት ላይ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለከንቲባው ያቀርባል፣

7. በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩት ነጋዴዎች ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት የሚሸጋገሩበትን አቅጣጫ ወይም ስትራቴጅ ይቀይሳል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል፣ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣
8. ለዚህ ደንብ ማስፈጸሚያ በቢሮው የሚወጡ ረቂቅ መመሪያዎች ላይ ይመክራል፣
9. አስተግባሪ አስፈጻሚ አካላት ለግብረ ኃይሉ ውሳኔ በሚያቀርቧቸው ሌሎች ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
10. የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት እና የውስጥ ደንብ ያወጣል፣
11. የዚህን ደንብ ማሻሻያ ሀሳቦችን ያቀርባል፡፡

25. ግብረ ኃይሉ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. ግብረ ኃይሉን በሰብሳቢነት ይመራል፣ የስብሰባ ጥሪ እንዲተላለፍ ያደርጋል፣ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ግብረ ኃይሉን ይወክላል፣
2. የግብረ ኃይሉ ስብሰባ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጥሪው ለግብረ ኃይሉ አባላት እንዲተላለፍ ያደርጋል፣
3. የግብረ ኃይሉ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
4. የግብረ ኃይሉ ውሳኔዎችና ሰነዶች በግብረ ኃይሉ ፀሐፊ አማካኝነት በሚገባ ተደራጅተው መያዛቸውን ይከታተላል፡፡

26. የግብረ ኃይሉ ስብሰባዎችና የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

1. ግብረ ኃይሉ በየወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣
2. ከግማሽ በላይ የሆኑ የግብረ ኃይሉ አባላት ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣
3. የግብረ ኃይሉ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ሆኖም የተሰጠው ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው የሚደግፈው የውሳኔ ሀሳብ ያልፋል፣
4. የግብረ ኃይሉ ውሳኔዎችና ሰነዶች በፀሐፊ አማካኝነት በሚገባ ተደራጅተው መያዛቸውን ይከታተላል፣



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

5. ስብሳቢው እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ አካላትን ግብረ ኃይሉ ስብሰባ ላይ በአስረጅነት እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይችላል፤

6. ግብረ ኃይሉ የራሱን የስብሰባና የአሰራር ሥነ-ስርዓት በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

27. <u>የደንቡ አስፈፃሚ አካላት ሚና</u>

ከዚህ በታች የተጠቀሱት የከተማዉ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ይህን ደንብ ለማስፈፀም እንደየድርሻቸው የሚከተለው ሚና ይኖራቸዋል፦

1. የንግድ ቢሮ ሚና

ሀ) በመደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ሊሳተፉ የሚችሉ ሰዎችን እና የመነገጃ ቦታዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ይለያል፣

ለ) የተለዩና መስፈርቱን የሚያሟሉ መደበኛ ያልሆኑ የጎዳና ላይ ነጋዴዎችን ይመዘግባል፣

ሐ) በጎዳና ላይ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በማህበር እንዲደራጁ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሰራል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣

መ) መደበኛ ያልሆነ የጎዳና ላይ የንግድ ሥራ በሥራ እድል ፈጠራ፣ በባዛር ማረጋጋት እና አጠቃላይ ለከተማዉ ኢኮኖሚ እድገት የሚኖረዉን አስተዋፅኦ ያጠናል ወይም እንዲጠና ያደርጋል፣

ሠ) በዘርፉ ለተሰማሩ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ቅድሚያ የመነገጃ ቦታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

ረ) ለመነገጃ ቦታ የሚከፈል የኪራይ መጠን ይወስናል፣

ሰ) መደበኛ ካልሆነ የጎዳና ላይ ንግድ ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት እንዲሸጋገሩ የሚያስችል ስልጠናዎችን ይሰጣል፣

2. የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ሚና

ሀ) የመነገጃ ቦታ ዝግጅት በተመለከተ የከተማዉ ፕላን በሚፈቅደዉ የመሬት አጠቃቀምና አግባብ ያላቸዉ ህጎችን መሰረት በማድረግ በዚህ ደንብ መሰረት በጎዳና ላይ ንግድ ለሚሰማሩ ሰዎች ቋሚና ጊዜያዊ የመነገጃ ቦታዎችን በማጥናት ይለያል፣ የመነገጃ ቦታ ያዘጋጃል፣ ይመድባል፣ ከቢሮዉ ጋር በመሆን መደበኛ ያልሆነ በጎዳና ላይ ንግድ ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች የሥራ ቦታ በጥንቃቄ ይፈቅዳል፣



Addis Ababa City

ለ) የሚያዘጋጃቸዉ ቋሚና ጊዜያዊ የመነገጃ ቦታዎች ከይገባኛል ጥያቄ ነፃ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

3. የትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ሚና

ሀ) ከከተማው የትራንስፖርት እና የትራፊክ እንቅስቃሴ ጋር አጣጥሞ መደበኛ ያልሆነ ወይም የእህድ ገበያ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራዎች የሚካሄድባቸውን መንገዶች የመለየት ሥራ ይሰራል፤ ምልክት ያደርጋል፤ የለያቸውን ለቢሮው ያሳውቃል፤ ከትራፊክ እንቅስቃሴ ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

ለ) መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ እንዲካሄድባቸው በተፈቀዱ መንገዶች ላይ የአደጋ መከላከያ ምልክቶች ያስቀምጣል፤ተቆጣጣሪ ባለሙያዎችን ይመድባል፤

4. የደንብ ማስከበር ባለስልጣን ሚና

ሀ) መደበኛ ያልሆነ ወይም የእህድ ገበያ ንግድ ሥራ በሚካሄድባቸዉ ጎዳናዎች፤ አደባባዮችን እና ክፍት ቦታዎች ላይ የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች የተመዘገቡና ፍቃድ ያላቸው መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያልተመዘገበ እና ያለ ፈቃድ ሲሰራ የተገኘ ሰዉ ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

ለ) ባልተፈቀዱ መንገዶች፤ አደባባዮች ፣ ክፍት ቦታዎች ላይ የጎዳና ላይ ንግድ እንዳይካሄድ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣

ሐ) በተፈቀዱ መንገዶች፤ አደባባዮች እና ክፍት ቦታዎች ላይ እንዲነግዱ በቢሮዉ የተፈቀደላቸዉ ሰዎች በተፈቀደለት ቀን፤ ሰዓት፤ ቦታና በተፈቀደለት የሥራ ዘርፍ መሰማራቱን፣ የከተማውን የውበት ደረጃ በጠበቀ መልኩ እየተካሄደ ስለመሆኑ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለቢሮዉ ያሳዉቃል፤

5. የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ሚና

ሀ) ኤጀንሲው ልዩ የጽዳት ፕሮግራም በማውጣት በዚህ ደንብ መሠረት የጎዳና ላይ ንግድ የሚካሄድባቸውን መንገዶችና አካባቢዎች መደበኛ የጽዳት የሥራ ጊዜውን ሳይጠብቅ ጽዳት ያካሄዳል፣

ለ) እንደአስፈላጊነቱ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎችን ያስቀምጣል፤ በወቅቱ ያነሳል፤

6. የአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን

ሀ) የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ይህን ደንብ ለማስፈጸም ቁጥጥር ሲያደርግ የፖሊስ ድጋፍ በሚያስፈልጉ ጉዳዮች ድጋፍ ያደርጋል፤

ለ) የጎዳና ላይ ንግድ ሥራ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ያለዉን ሰላምና ፀጥታ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስከብራል፤

7. የምግብና መድሃኒት ባለሥልጣን

ባለስልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት በጎዳና ላይ ለሽያጭ የሚቀርቡ ምግቦችን አስመልክቶ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከጤንነት ጋር በተያያዘ ቁጥጥር ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

28.ስለተጠያቂነት

ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ሲገኝ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

29.በአስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ

በዚህ ደንብ መሠረት በክፍለ ከተማው ወይም በወረዳው ጽሕፈት ቤት አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት ማንኛውም ሰው፡-

1. እርምጃው ከተወሰደበት ወይም ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በአስተዳደራዊ እርከን ደረጃ ተዋረዱን በመጠበቅ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት፣ ለክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ወይም ለቢሮው አቤቱታ በጽሑፍ ሊያቀርብ ይችላል፤
2. አቤቱታ የቀረበለት አካል በ10 (አስር) የሥራ ቀናት ውስጥ ለቀረበለት አቤቱታ ውሳኔውን በጽሑፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሣወቅ አለበት፡፡

30.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

31.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ከግብረ ኃይሉ ጋር በመመካከር ሊያወጣ ይችላል፡፡



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ Addis Ababa City Administration Justice Bureau

## 32. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣው ደንብ ቁጥር 88/2009 ዓ.ም በዚህ ደንብ ተሽሯል፤

2. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማው አስተዳደር ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 33. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከየካቲት 29 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት 29 ቀን 2017 ዓ.ም

አዳነች አቤቤ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

